

# የወሊድ መቆጣጠሪያ ምርጫዎች

| ዘዴ | አጠቃቀም | በደም መፍሰስ ላይ ያለው ተጽእኖ | መታወቅ ያለባቸው ነገሮች | ምን ያህል ውጤታማ ነው?* |
|---|---|---|---|---|
| **በመርፌ የሚሰጥ/ዘ ሻት/**<br>ዲፖ-ፕሮቬራ®<br> | • በየ3 ወሩ (በየ13 ሳምንቱ) መርፌ ይወጋሉ<br>• መርፌውን እራሰዎ ወይም የህክምና ባለሙያ ሊወጋዎ ይችላል | • ብዙ ጊዜ የወር አበባ ፍሰት ይቀንሳል<br>• ጠብታ ደም ሊያዩ ወይም የወር አበባዎ ሊቋረጥ ይችላል | • አንዱ መርፌ እስከ 15 ሳምንታት ድረስ ይሰራል<br>• የግል የሆነ<br>• የማህጸን ካንሰርን ለመከላከል ይረዳል<br>• የሰውነት ክብደት መጨመር፣ ድብርት፣ የፀጉር ወይም የቆዳ ለውጥ፣ የወሲብ ፍላጎት ለውጥን ሊያስከትል ይችላል<br>• የማኅጸን ሽፋን ካንሰር፣ የማህፀን ካንሰር እና የፖሊሰቲክ ኦቫሪ ሲንድሮም (PCOS) ስጋትን ሊቀንስ ይችላል<br>• መርፌውን ካቆሙ በኋላ የኀንዮሽ ችግሮች እስከ 6 ወራት ድረስ ሊቆዩ ይችላሉ | 96% |
| **የመፅነስ ቀናት ግንዛቤ**<br>ተፈጥሮኣዊ የቤተሰብ ምጣኔ<br> | • የመፅነስ ቀናትን ይተንብዩ፡ በየቀኑ የሙቀት መጠንን በመውሰድ፣ የሴት ብልትን ፈሳሽ ለውጦችን በመፈተሽ፣ እና/ወይም የወር አበባዎን በመመዝገብ<br>• ከእነዚህ ዘዴዎች ውስጥ ከአንድ በላይ መጠቀም የተሻለ ውጤት ያስገኛል<br>• ማርገዝ በሚቹልባቸው ቀናት የግብረ ሥጋ ግኙኙነትን **ከመጠቀም ይቆጠቡ** ወይም ኮንዶም/ስፐርሚሳይድ ይጠቀሙ | • የወር አበባዎ መደበኛ ካልሆነ በደንብ አይሰራም | • ዋጋው አነስተኛ ነው<br>• እርግዝናን ለመከላከል ወይም ለመፅነስ ይረዳል<br>• በመፅነሻ ቀናትዎ የተለየ ዘዴ ይጠቀሙ<br>• ይህ ዘዴ ብዙ ጥረት ይጠይቃል<br>• የሐኪም ማዘዣ አያስፈልግም | 85% |
| **ቆዳ ላይ የሚለጠፍ/ፓች/**<br>ኦርቶ ኤቭራ®<br> | • ለሶስት ሳምንታት በሳምንት አንድ ጊዜ አዲስ ፓች ይጠቀሙ<br>• በ4ኛው ሳምንት ምንም ፓች ኣይጠቀሙ | • የወር አበባዎ የበለጠ መደበኛ እና ያነሰ ህመም እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል<br>• በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ የደም መንጠባጠብን ሊያስከትል ይችላል። | • ፓች ማድረግ ካቆሙ በኋላ ወዲያውኑ ማርገዝ ይችላሉ<br>• በፓች ስር ያለ ቆዳን ሊያስቆጣ ይችላል<br>• ይህ ዘዴ ኤስትሮጅንን ይይዛል - ኤስትሮጅን ከቴስቶስትሮን ጋር ይገናኝ እንደሆነ ግልጽ አይደለም | 93% |
| **የሴት የማምከኛ ዘዴ፡ በትቦ ላይ የሚደረጉ ዘዴዎች/Tubal Methods/**<br> | • እነዚህ ዘዴዎች የፋሎፒያን ቱቦች በምዝጋት ወይም በመቁረጥ ይከናወናሉ<br>• ሐኪሙ የፋሎፒያን ቱቦች ለመድረስ ሆድዎን መብጣት አለበት | ምንም | • እነዚህ ዘዴዎች ቋሚ እና በጣም ውጤታማ ናቸው<br>• መቀልበስ ከባድ ነው<br>• አደጋዎቹ ኢንፌክሽን፣ ደም መፍሰስ፣ ህመም እና የማደንዘዣ አለመቀበልን ያካትታሉ | > 98% |

* የተለመደ አጠቃቀም

የሰነ-ተዋልዶ ጤና ተደራሽነት ፕሮጀክት / ጥቅምት 2022


www.reproductiveaccess.org
www.unityhealthcare.org

| ዘዴ | አጠቃቀም | በደም መፍሰስ ላይ ያለው ተጽእኖ | መታወቅ ያለባቸው ነገሮች | ምን ያህል ውጤታማ ነው?* |
|---|---|---|---|---|
| **የዉንድ የማምከኛ ዘዴ፡ ቫሴክቶሚ**<br> | • ሐኪም ከወንድ የዘር ፍሬዎ ላይ ስፐርም የሚወስዱትን ቱቦዎች ይዘጋቸዋል ወይም ይቆርጣቸዋል | ምንም | • ይህ ዘዴ ቋሚ እና በጣም ውጤታማ ነው<br>• ከቱባል ዘዴዎች የበለጠ ውጤታማ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተመጣጣኝ ነው<br>• በሐኪሙ ቢሮ ውስጥ ሊከናወን ይችላል<br>• አጠቃላይ ማደንዘዣ አያስፈልግም<br>• መቀልበስ ከባድ ነው<br>• ስጋቶች ኢንፌክሽን፣ ህመም እና ደም መፍሰስ ያካትታሉ<br>• ለመስራት እስከ 3 ወር ድረስ ይወስዳል | > 99% |
| **ከሴት ብልት ማስወጣት**<br>በማስወጣት | • የዘር ፈሳሽ ከመውጣቱ በፊት የወንድ ብልትን ከሴት ብልት ያውጡ (ማለትም ከመምጣቱ በፊት) | ምንም | • ምንም ዋጋ ኣያስወጣም<br>• ለአንዳንድ ሰዎች ላይ የወሲብ ደስታን ሊቀንስ ይችላል<br>• ብልት በጊዜ ካልወጣ አይሰራም<br>• የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማቋረጥ አለበት | 80% |
| **ቀለበት/ዘ ሪንግ/**<br>እኖቬራ®<br>ኑቫሪንግ®<br> | • ትንሽ ቀለበት ወደ ብልት ውስጥ ያስገቡ<br>• ወርሃዊ ቀለበት፡ በየወሩ ቀለበት ይቀይሩ<br>• ኣመታዊ ቀለበት፡ በየአመቱ ቀለበት ይቀይሩ | • የወር አበባዎ የበለጠ መደበኛ እና ያነሰ ህመም እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል<br>• በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ የደም መንጠባጠብን ሊያስከትል ይችላል።<br>• የሴት ብልት ፈሳሽ መጨመር ሊያስከትል ይችላል። | • ሁለት ዓይነት አሉ፦ ወርሃዊ ቀለበት እና ዓመታዊ ቀለበት።<br>• ለሁሉም ሰው መጠኑ አንድ አይነት ነው<br>• የግል የሆነ<br>• ቀለበቱን ማድረግ ካቆሙ በኋላ ወዲያውኑ ማርገዝ ይችላሉ<br>• ይህ ዘዴ ኤስትሮጅንን ይይዛል - ኤስትሮጅን ከቴስቶስትሮን ጋር ይገናኛ እንደሆነ ግልጽ አይደለም | 93% |
| **ተከላ ወይ ኢምፕላንት**<br>ኔክስፕላኖን ®<br> | • የጤና ባለሙያ በላይኛው ክንድዎ ቆዳ ስር ይቀብረዋል<br>• ዘዴውን ማቆም ከፈለጉ ሀኪም ያወጣልዎታል | • መደበኛ ያልሆነ የደም መፍሰስ እና የደም መንጠባጠብ ሊያስከትል ይችላል<br>• ከ 1 አመት በኋላ የወር አበባዎ ሊቋረጥ ይችላል<br>• ቁርጠቱ ከጊዜ በኋላ እየተሻሎት ይሄዳል | • ለረጅም ጊዜ የሚቆይ (እስከ 5 ዓመታት)<br>• ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ ማርገዝ ይችላሉ<br>• የማኅጸን ሽፋን ካንሰር፣ የማህፀን ካንሰር እና የፖሊስቲክ ኦቫሪ ሲንድሮም (PCOS) ስጋትን ሊቀንስ ይችላል<br>• የስሜት ለውጦችን ሊያስከትል ይችላል | > 99% |
| **ኣዩዲ፡ ሆርሞን ያለው**<br>ሊለታ®፣ ሚሬና®፣ ስካይላ® እና ሌሎች<br> | • በማህፀን ውስጥ በህክምና ባለሙያ መቀመጥ አለበት<br>• ኣብዛኛው ጊዜ በሃኪም መውጣት አለበት። | • ቁርጠት እየተሻሻለ ይሄዳል<br>• ቀለል ያለ የወር አበባ፣ የደም ጠብታ ወይም የወር አበባ ሊቋረጥ ይችላል | • ሌቮኖርጌስትረል ፕሮጄስትሮን ይጠቀማል<br>• በመረጡት የኣዩዲ ኣይነት የሚወሰን ሆኖ ከ3 እስከ 8 ዓመታት በውስጥ ሊቆይ ይችላል<br>• ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ ማርገዝ ይችላሉ<br>• የማኅጸን ሽፋን ካንሰር፣ የማህፀን ካንሰር እና የፖሊስቲክ ኦቫሪ ሲንድሮም (PCOS) ስጋትን ሊቀንስ ይችላል<br>• አልፎ አልፎ፣ ሀኪሙ በሚቀመጥበት ጊዜ የማህጸን ጉዳት ሊያጋጥም ይችላል | > 99% |

* የተለመደ አጠቃቀም

| ዘዴ | አጠቃቀም | በደም መፍሰስ ላይ ያለው ተጽእኖ | መታወቅ ያለባቸው ነገሮች | ምን ያህል ውጤታማ ነው?* |
|---|---|---|---|---|
| **ኣዩዲ፡ ኮፐር**<br>ፓራጋርድ®<br> | • በማህፀን ውስጥ በህክምና ባለሙያ መቀመጥ አለበት<br>• ኣብዛኛው ጊዜ በሃኪም መውጣት አለበት። | • ቁርጠት እና ከባድ የወር አበባ ሊያስከትል ይችላል<br>• በወር አበባ መካከል የደም መንጠባጠብን ሊያስከትል ይችላል (ቴስቶስትሮን ከወሰዱ ይህ ችግር ላይሆን ይችላል) | • እስከ 12 ዓመታት ያገለግላል<br>• ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ ማርገዝ ይችላሉ<br>• የማኅጸን ሽፋን ካንሰር፣ የማህፀን ካንሰር እና የፖሊስቲክ ኦቫሪ ሲንድሮም (PCOS) ስጋትን ሊቀንስ ይችላል<br>• አልፎ አልፎ፣ ሀኪሙ በሚቀመጥበት ጊዜ የማህጸን ጉዳት ሊያጋጥም ይችላል | > 99% |
| **ክኒን**<br> | • ክኒኑን በየቀኑ ይውሰዱ | • ለብዙ ወራት የሚቆይ የደም መንጠባጠብ ሊያጋጥም ይችላል | • የPMS ምልክቶችን ሊያሻሽል ይችላል<br>• ብጉርን ሊያሻሽል ይችላል<br>• የማህጸን እንቁላል ካንሰርን ለመከላከል ይረዳል<br>• ይህ ዘዴ ኤስትሮጅንን ይይዛል - ኤስትሮጅን ከቴስቶስትሮን ጋር ይገናኝ እንደሆነ ግልጽ አይደለም<br>• ክኒኑ መውሰድ ካቆሙ በኋላ ወዲያውኑ ማርገዝ ይችላሉ<br>• ማቅለሽለሽ፣ክብደት መጨመር፣ራስ ምታት፣የወሲብ ፍላጎት መቀየር ሊያስከትል ይችላል - አንዳንዶቹ ወደ ሌላ አይነት ክኒን በመቀየር መፍትሄ ያገኛሉ | 93% |
| **የሴት ኮንዶም**<br> | • የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈፀሙ ቁጥር አዲስ ኮንዶም ይጠቀሙ<br>• እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ቅባት ይጠቀሙ | ምንም | • የወሲብ ጨዋታ/የቅድመ-ወሲብ ጨዋታ አካል አድርጎ መጠቀም ይቻላል<br>• በፊንጢጣ እና በሴት ብልት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መጠቀም ይቻላል<br>• በሴት ብልት/ፊንጢጣ ደስታን ይጨምራል<br>• የሌቴክስ አለርጂ ላለባቸው ሰዎች ጥሩ ነው<br>• ከኤችአይቪ እና ከሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ይከላከላል<br>• የወንድ ብልት ስሜትን ይቀንሳል<br>• ድምጹ ሊረብሽ ይችላል<br>• ለማስገባት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል<br>• በወሲብ ወቅት ተንሸራቶ ሊወልቅ ይችላል<br>• ከጤና አቅራቢዎ የሐኪም ማዘዣ አይፈልግም | 79% |
| **የወንድ ኮንዶም**<br> | • የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈፀሙ ቁጥር አዲስ ኮንዶም ይጠቀሙ<br>• ለላቲክስ አለርጂክ ካለብዎት የፖሊዩረቴን ኮንዶም ይጠቀሙ። | ምንም | • በብዙ ሱቆች መግዛት ይቻላል<br>• የወሲብ ጨዋታ/የቅድመ-ወሲብ ጨዋታ አካል አድርጎ መጠቀም ይቻላል<br>• የዘር ፈሳሽ ቶሎ መፍሰስን ለመከላከል ይረዳል<br>• በአፍ፣ በሴት ብልት እና በፊንጢጣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መጠቀም ይቻላል<br>• ከኤችአይቪ እና ከሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ይከላከላል<br>• የወንድ ብልት ስሜትን ይቀንሳል<br>• የብልት ኣለመቆምን ሊያስከትል ይችላል<br>• ሊቀደድ ወይም ተንሸራቶ ሊወልቅ ይችላል<br>• የሐኪም ማዘዣ አያስፈልግም | 87% |
| **ዲያፍራም**<br>ካያ® እና ሚሌክስ®<br> | • የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈፀሙ ቁጥር የሴት ብልት ውስጥ የሚቀመጥ<br>• በእያንዳንዱ ጊዜ የዘር ፍሬን ከሚያጨነግፍ ቅባት ጋር ይጠቀሙ | ምንም | • ለብዙ አመታት ሊቆይ ይችላል<br>• በአነስተኛ ክፍያ መጠቀም ይቻላል<br>• ከአንዳንድ ኢንፌክሽኖች ሊከላከል ይችላል፣ ነገር ግን ኤችአይቪን አይከላከልም<br>• ስፐርሚሳይድ (የወንዴ ዘር ገዳይ) መጠቀም ለኤችአይቪ የመጋለጥ እድልን ይጨምራል<br>• ከሴት ብልት ደም መፍሰስ ወይም ኢንፌክሽን በሚኖር ጊዜ አይጠቀሙ<br>• በሽንት ፊኛ ኢንፌክሽን የመያዝ እድልን ይጨምራል | 83% |

* የተለመደ አጠቃቀም

| ዘዴ | አጠቃቀም | በደም መፍሰስ ላይ ያለው ተጽእኖ | መታወቅ ያለባቸው ነገሮች | ምን ያህል ውጤታማ ነው?* |
|---|---|---|---|---|
| **ለድንገተኛ እርግዝና መከላከያ ክኒኖች**<br>ፕሮጄስቲን EC (እቅድ B® ዋን ስቴፕ እና ሌሎች) እና ዩሊፕሪስታል ኣስቴት (ኤላ®)<br> | • ጥንቃቄ ካልተደረገበት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በኋላ ቶሎ ሲወሰዱት በተሻለ ሁኔታ ይሰራል<br>• EC ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ ባሉት እስከ 5 ቀናት ድረስ መጠቀም ይቻላል<br>• ማሸጊያው 2 እንክብሎችን ከያዘ፣ ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ይውሰዱ | • የሚቀጥለው የወር አበባዎ ቀደም ብሎ ወይም ዘግይቶ ሊመጣ ይችላል<br>• እጅግ አነስተኛ የደም መፍሰስ ሊያስከትል ይችላል | • በፋርማሲዎች፣ በጤና ጣቢያዎች፣ ወይም በጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ይገኛል፡ መኖሩን ለማረጋገጥ አስቀድመው ይደውሉ<br>• በማንኛውም እድሜ ላይ ያሉ ሰዎች ያለ ማዘዣ ፕሮጄስቲን EC ሊያገኙ ይችላሉ<br>• የሆድ ድርቀት ወይም ማቅለሽለሽ ሊያስከትል ይችላል<br>• ፕሮጄስቲን EC ከቴስቶስትሮን ጋር መስተጋብር የለውም፣ ነገር ግን ዩሊፕሪስታል ኣስቴት EC መስተጋብር እንዳለው እና እንደሌለው አናውቅም<br>• ዩሊፕሪስታል ኣስቴት EC የሐኪም ማዘዣ ያስፈልገዋል<br>• ብዙ ወጪ ሊጠይቅ ይችላል<br>• የሰውነትዎ ክብደት መረጃ ጠቋሚ (BMI) ከ26 በላይ ከሆነ ዩሊፕሪስታል ኣስቴት EC ከፕሮጄስትሮን EC የተሻለ ይሰራል።<br>• ዩሊፕሪስታል ኣስቴት EC ከወሲብ በኋላ ከ3-5 ቀናት ቢወሰድ ከፕሮጀስቲን EC የተሻለ ይሰራል | 58 - 94% |
| **የሴትን ብልት አሲዳማ የሚያደርግ ጄል**<br>ፌክሲ®<br> | • የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈፀሙ ቁጥር የሴት ብልት ውስጥ ጄል ያስቀምጡ | ምንም | • የወሲብ ጨዋታ/የቅድመ-ወሲብ ጨዋታ አካል አድርጎ መጠቀም ይቻላል<br>• ምንም አይነት ሆርሞኖች የሉትም<br>• የሐኪም ማዘዣ ያስፈልገዋል<br>• የሴት ብልትን፣ የወንድ ብልትን፣ ሊለበልብ ይችላል<br>• የሽንት ቱቦ ኢንፌክሽን ሲኖር ጥቅም ላይ አይውልም | 86% |
| **የወንዴ ዘር ገዳይ በሴት ብልት ውስጥ (ቨጂይናል ስፐርምሳይድ)**<br>ክሬም፣ ጄል፣ ስፖንጅ፣ አረፋ፣ ወደ ብልት የሚገባ፣ ፊልም<br> | • የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈፀሙ ቁጥር ስፐርምሳይድን ያስገቡ | ምንም | • በብዙ ሱቆች መግዛት ይቻላል<br>• የወሲብ ጨዋታ/የቅድመ-ወሲብ ጨዋታ አካል አድርጎ መጠቀም ይቻላል<br>በብዙ መልክ ይመጣል፡ ክሬም፣ ጄል፣ ስፖንጅ፣ አረፋ፣ ወደ ብልት የሚገባ፣ ፊልም<br>• ለኤችአይቪ የመጋለጥ እድልን ሊጨምር ይችላል<br>• የሴት ብልትን፣ የወንድ ብልትን፣ ሊለበልብ ይችላል<br>• ክሬም፣ ጄል እና አረፋ የተዝረከረከ ሊሆን ይችላል<br>• የሐኪም ማዘዣ አያስፈልግም | 79% |
| **ፕሮጄስቲን-ክኒኖችን ብቻ**<br> | • ክኒኑን በየቀኑ ይውሰዱ | • የወር አበባዎ የበለጠ መደበኛ እና ያነሰ ህመም እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል<br>• በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ የደም መንጠባጠብን ሊያስከትል ይችላል። | • ክኒኑ መውሰድ ካቆሙ በኋላ ወዲያውኑ ማርገዝ ይችላሉ<br>• የማኅጸን ሽፋን ካንሰር፣ የማህፀን ካንሰር እና የፖሊስቲክ ኦቫሪ ሲንድሮም (PCOS) ስጋትን ሊቀንስ ይችላል<br>• የመንፈስ ጭንቀት፣ የፀጉር ወይም የቆዳ ለውጥ፣ የወሲብ ፍላጎት መቀየርን ሊያስከትል ይችላል | 93% |

*** የተለመደ አጠቃቀም**